17ኛ ዓመት ቁጥር 14
17th Year No. 14

ባህር ዳር ሐምሌ 1ቀን 2004 ዓ/ም
Bahir Dar July 8, 2012

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
# የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት
# ዝክረ ሕግ
# ZIKRE HIG
## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 95
Unit price 95

| ማውጫ | Content |
| --- | --- |
| **አዋጅ ቁጥር196/2004 ዓ.ም.** | **Proclamation Number 196/2012** |
| በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የ2004 እና የ2003 በጀት አመት ለመንግስት ሥራዎች ማስፈጸሚያ ተጨማሪ በጀትን ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ | A Proclamation Issued to Provide for the Approval of Supplementary Budget for the implementation of the 2011 and 2010 Budget Year Government Activities in the Amhara National Regional State |

## አዋጅ ቁጥር 196/ 2004 ዓ.ም.

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የ2004 እና የ2003 በጀት አመት ለመንግስት ሥራዎች ማስፈጸሚያ ተጨማሪ በጀት ማጽደቂያ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት መሠረት ክልሉ የራሱን በጀት የማፅደቅና ሥራ ላይ የማዋል ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 (1) እና በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ 178/2003 (እንደተሻሻለው) አንቀፅ 27 ድንጋጌዎች ስር በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚከተለውን አውጇል፡፡

## Proclamation Number 196/ 2012

**The Amhara National Regional State Supplementary Budget for the Government Activities of the 2011 and 2010 Budget Year Approval Proclamation**

Whereas, in accordance with the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, the Region is vested with the power to approve and implement its Budget;

Now, therefore, the Council of the Amhara National Region, in accordance with the power vested in it under the provisions of Sub-Article 3/1/ of Article 49 of the Revised Constitution of the National Region and Article 27 of the Regional Finance Administration Proclamation No. 178/2011 (as amended) , hereby proclaims as follows.

1. **<u>አጭር ርዕስ ፦</u>**

ይህ አዋጅ «በ2004 እና በ2003 የበጀት ዓመት ለመንግሥት ሥራዎች ማስፈፀሚያ የታወጀ የተጨማሪ በጀት አዋጅ ቁጥር 196/2004 ዓ.ም» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. የ2003 የበጀት አመት ወረዳዎች ዘግይተው በማቅረባቸው ሳይታወጅ የቀረ ነገር ግን ጥቅም ላይ የዋለ ገቢና ወጭ

**ሀ.** ገቢ ብር 44,715,956.12

2.1. የወረዳና የከተማ አስተዳደር ገቢ ብር 44,715,956.12

**ለ.** ወጪ ብር 44,715,956.12

2.2. ለወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች መደበኛ ወጪ ብር 44,715,956.12

3. <u>በ2004 በጀት አመት ለተጨማሪ ስራዎች ማስፈጸሚያ የዋለ ገቢና ወጪ</u>

3.1. ለ2004 በጀት ዓመት ተጨማሪ ስራዎች የዋለ ገቢ

ሀ. ከ2003 በጀት ዓመት የዞረ ከወጪ ቀሪ ብር 60,600,000 (ስድሣ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺ ብር)፣

ለ. የግብርና ቢሮ Gov.69 ሲዘጋ የተገኘ ብር 3,210,686

ሐ. ከዕቅድ በላይ በወረዳ እና ከተማ አስተዳደር የተሰበሰበ ገቢ ብር 98,998,826 (ዘጠና ስምንት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ዘጠና ስምንት ሺ ስምንት መቶ ሀያ ስድስት ብር)

መ. የውስጥ ገቢ ሰብስበው እንዲጠቀሙ ከተፈቀደላቸው ክልል ተጠሪ መስሪያ ቤቶች ከዕቅድ በላይ የተሰበሰበ ገቢ ብር 19,456,651 (አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን አራት መቶ ሃምሳ ስድስት ሺ ስድስት መቶ ሃምሳ አንድ ብር) ድምር ብር 182,266,163 (አንድ መቶ ሰማኒያ ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ስድሳ ስድስት ሺ አንድ መቶ ስድሳ ሶስት ብር)



**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as "the Amhara National Regional State Supplementary Budget for the Government Activities of the 2011 and 2010 Budget Year Approval Proclamation No.196/2012"

**2.** The 2011 Budget Year, utilized without being proclaimed due to the delay on the part of Woredas, revenue and expenditure

**A.** Revenue 44,715,956.12

2.1. Revenue of Woreda and City Administration Birr 44,715,956.12

B. Expenditure 44,715,956.12

2.2. Regular Expenditure for Woredas and City Administrations Birr 44,715,956.12

**3.<u>Revenue and expenditure utilized in the 2011 Budget Year for the implementation of supplementary activities</u>**

**3.1** Revenue for supplementary activities in the 2011 Budget Year

A. Revolve from the 2011 Budget Year Birr 60,600,000/ sixty million six hundred thousand birr/

B. Amount found while the Gov. 69 of the Bureau of Agriculture closed Birr 3,210,686

C. Revenue collected by woreda and city administrations beyond plan Birr 98,998,826/ Ninety Eight million nine hundred ninety eight thousand eight hundred twenty six/

D. Revenue collected beyond plan by regional accountable Offices authorised to utilise same Birr 19,456,651/ ninety million four hundred fifty six thousand six hundred fifty one/ Total Birr 182,266,163/ one hundred eighty two million two hundred sixty six thousand one hundred sixty three/

3.2. **<u>ወጪ</u>**

ለ2004 በጀት አመት ለመንግስት ተጨማሪ ስራዎች የዋለ ወጭ ብር 182,266,163 (አንድ መቶ ሰማኒያ ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ስድሳ ስድስት ሺ አንድ መቶ ስድሳ ሶስት ብር) ሲሆን ዝርዝሩም

3.2.1. ለወረዳዎች ለሰኔ ወር ደመወዝ በብድር የተሰጠ ብር 38,425,395

3.2.2. በተለያዩ ጊዜያት ከመጠባበቂያ ለወረዳዎች እና ለቢሮዎች የተደገፈ ብር 72,850,865

3.2.3. ወረዳዎች የተጠቀሙበት 50% ድርሻ ብር 51,533,252

3.2.4. ክልል ተጠሪ መስሪያ ቤቶች ከውስጥ ገቢ የተሰበሰበና ለተለያዩ ተግባራት የዋለ ወጭ ብር 19,456,651

4. **<u>የአዋጁ ተፈጻሚነት</u>**

የ2004 በጀት ዓመት በጀትን ለማወጅና የበጀቱን አስተዳደር ለመወሰን በወጣው አዋጅ የተሰጠው ሥልጣን በዚህ አዋጅም ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

5. **<u>አዋጁ የሚፀናበት ቀን</u>**

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህር ዳር

ሐምሌ 1 ቀን 2004 ዓ.ም

አያሌው ጎበዜ

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዚደንት



**3.2. <u>Expenditure</u>**

Expenditure implemented for the 2011 Budget Year supplementary Government activities is Birr 182,266,163/ one hundred eighty two million two hundred sixty six thousand one hundred sixty three/; and the particulars are:

3.2.1. Loan granted to woredas for salary of the Month of Sene Birr 38,425,395

3.2.2. Subsidy made to Woredas and the Bureaus in different times from the reserved fund Birr 72,850,865

3.2.3. 50% share utilized by Woredas Birr 51,533,252

3.2.4. Expenditure, which has been collected from the internal revenue of Regional accountable Offices, utilized for various activities Birr 19,456,651

**4. <u>Applicability of the proclamation</u>**

The power vested in by virtue of the approval of the 2011 Budget Year Budget and its administration proclamation shall, *mutatis mutandis*, apply to this proclamation.

**5. <u>Effective Date</u>**

This proclamation shall come in to force as of the date of its publication in the Zikre- Hig Gazzette of the Regional State.

Done at Bahir Dar,

This 8th day of July, 2012.

Ayalew Gobezie

President of Amhara National Regional State